# በጎንደር የሱዳኖችን ጥቃት በተመለከተ

ግርማ ካሳ - ሜይ 2 2008
(muziky68@yahoo.com)



"አጼ ዮሐንስ ይዋሻሉ
መጠጥ አልጠጣም ይላሉ
ሲጠጡ አይናቸው በርግጥ
እራስ የሚያዞር መጠጥ"

ይህ ለአጼ ዮሐንስ አራተኛ የተገጠመ ቅኔ ነበር። ሰሙ፣ አጼ ዮሐንስ መጠጥ አልጠጠም እያሉ የሚያሰክር መጠጥ ሲጠጡ እንዳደታዩ የሚገልጽ ሲሆን የቅኔው ዋና መልእክት፣ ወርቁ ግን፣ የእኚህን ታላቅ ኢትዮጵያዊ የደም መስዋዕትነት ያሳያል።

በቅርቡ የሱዳን ወታደሮች በኢትዮጵያ ድንበር ዘልቀው በመግባት ከተሞቻችንና መንደሮቻችንን እያቃጠሉ እንደሆነ በስፊው እየተዘገበ ነው። የሱዳን ታጣቂዎች በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጽሙት እኩይ ተግባር አሁን በኦማር አልባሽር አገዛዝ የተጀመረ አይደለም።

ከመቶ አመታት በፊት ማህዲስት ደርቡሾች (ሱዳኖች) እስከ ጎንደር ከተማ በመዝለቅ ትልቅ ቃጠሎ እንዳደረሱ ታሪክ ያስተምረናል። በወቅቱ የኢትዮጵይ ርዕሰ ብሄር የነበሩት አጼ ዮሐንስ አራተኛ ይህን ድንበር ዘለል ጥቃት ለመመከት ወዲያው ነበር ወደ ጎንደር የተሰማሩት። እራሳቸው የሚመሩትን ጦር በማዝመት ማህዲስቶችን በጀግንነት ከኢትዮጵያ ምድር ገፍተው ወደ ሱዳን ድንበር አደረሷቸው።

አጼ ዮሐንስ ፣ ሌላውን አስቀድመው ከኋላ መቅረት ይችሉ ነበር። ነገር ግን "በአገር ጉዳይ ላይ ወደኋላ ማለት የለም" በሚል ቁርጠኝነት ከተራው ወታደር እኩል እፊት ፊት ቀደሙ። ሙሉ ለሙሉ ፍልሚያው ውስጥ ገቡ።

ታዲያ የኢትዮጵያ ሰራዊት በድል ወደፊት እየገሰገሰ ባለበት ወቅት ድንገት ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ይመቱና ሱዳን ድንበር አካባቢ መተማ ላይ እኚህ ጀግና፣ አንበሳ፣ ታላቅ የኢትዮጵያ ልጅ ለአገራቸው ነጻነትና አንድነት ሲሉ ይወድቃሉ። አጼ ቴዎድሮስ በመቅደላ ተራራ ላይ በእንግሊዞች እጅ ላለመማረክ ጥይት ጠጥተው እራሳቸውን በገደሉ ጊዜ ተገጥሞ የነበረውን ግጥም ትንሽ ለውጥ አድርጌ ፡

" መተማ ሜዳ ላይ ጨኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ"

ስል የእኚህን ኩሩ ኢትዮጵያዊ ገድል እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ በዚህ አጋጣሚ እዘክረዋለሁ።

ከዚያ በኋላ በአጼ ዮሐንስ መሞት የኢትዮጵያ ሰራዊት ደነገጠ። ማህዲስት ደርቡሾች አይለው መጡ። የአጼ ዮሐንስን እራስ ቆርጠው በምድራቸው እያዞሩ ነጋሪት አስነፉ።

በአሁኑ ወቅትም የሱዳን ታጣቂዎች ያኔ በአጼ ዮሐንስ ዘመን እንዳደረጉት ሁሉ በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት እያደረሱ ነው። በኢትዮጵያ ያሉ መሪዎች ግን የሚመልሱት ምላሽ ያኔ አጼ ዮሐንስ ከመለሱት ምላሽ ጋር ሲነጻጸር ሰማይና ምድር የተራራቀውን ያህል የተራራቀ ነው።

እስከአሁን ድረስ ኢሕአዴግ ሙሉ ለሙሉ ከሚቆጣጠራቸው የመገናኛ ብዙሃን፣ በጎንደር መንደራቸው በሱዳን አሸባሪዎች ስለተቃጠለባቸው ወገኖቻችን የተዘገበ አንዳች ነገር የለም። ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ሆነ ከጠቅላይ ሚኒስቱ ጽ/ቤት የወጣ መግለጫ አላነበብንም። በውጭ አገር ባሉ እንደ አይጋ ፎረም (የኢትዮጵያ ራሽ ሊምቦ) እና ኢትዮጵያ ፈርስት የተሰኙ አፍቃሪ ኢሕአዴግ ድህረ ገጾች ዘንድም አምስት ሳንቲም አልተጻፈም።

የሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች መሪ የነበሩ ሼክ አዌ "በኢትዮጵያ ላይ ጅሃድ አውጃለው" በማለታቸው ብቻ የአገራችንን ሉዓላዊነትና አንድነት ማስጠበቅ አለብን በሚል ሰበብ፣ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሱማሌን እንዲወር መደረጉ

የሚታወስ ነው። ኢትዮጵያውያን በታሪካችን ጎሮቤት አገር ወረን አናቅም። እነ አቶ መለስ ዜናዊ አስጀመሩን።

ታዲያ በሰፊው እየተዘገበ ያለውን የኢትዮጵያ ዳርፉር በተመለከተ ከኢሕአዴግ ዘንድ ዝምታ ብቻ ነው ያየነው። **የሱዳን አሸባሪዎች የሚፈነጩበት አካባቢ የአጼ ዮሐንስ አስክሬንና የመይሳው ካሳ አጼ ቴዎድሮስ እትብት የተቀበረበት፣ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረ አይደለም እንዴ ? ታዲያ ዝምታው ለምንድን ነው ?**አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አሠማም እንደተባለው ሳይሆን እንደማይቀር እገምታለሁ።

በሶማሊያ ጦርነት ለማወጅ ሲባል ሲለፈፍብን የነበረው ለ"ኢትዮጵያ አንድነት የመቆርቆሩ ጉዳይ" አሁን ወደት ነው ያለው ? ወይስ የኢትዮጵያ ጥቅም የግልሰብን ጥቅም ከሚያስጠብቅ የውጭ ሃይል ጥቅም ያነሰ ነው ?

በፓርላማ ተቀምጠው ተቃዋሚ ነን የሚሉ እነ አቶ ልደቱ አያለውና ዶር በየነ ጰጥሮስን የመሳሰሉ "ታማኝ" ተቃዋሚዎች እነርሱም ዝምታን የመረጡ ይመስላል። ኢሕአዴግን እንዳያኮርፍና በፓርላማ አቶ መለስ ዜናዊ እንዳይወርፏቸው ፈርተው ይሆን? መልሱን ለእነርሱ እተዋለሁ።

ያኔ የኢትዮጵያ ርእሰ ብሄር የነበሩት ጃንሆይ አጼ ዮሐንስ አራተኛ፣ ደማቸውን ለኢትዮጵያ ሲያፈሱ የአሁኑ ርእሰ ብሄር ግን ለኢትዮጵያም ደንታም ያላቸው አይመስልም። የአፋሩ ሱልጣን ኢብራሂም አሰብን በገንዝብ እንደሸጡ ሁሉ በአራት ኪሎ ያሉ መሪዎችም ድንገት ከሱዳን ነዳጅ ለማግኘት ወይንም በሱዳን በትጥቅ ትግል የሚታገሏቸው ካሉ ቦታ እንዳያገኙ ለማከላከል አሊያም በኤርታራ በኩል የባህር በር ስለተዘጋና የበርበራን ወደብ የመጠቀሙ ጉዳይም አስተማማኝ ሰላልሆነ የሱዳን ወደብን ለመጠቀም አስበው ይሆን የዳርፋሩን ወንጀለኛ ኦማር አልባሽርን አቅፈው የሚያስተናግዱት? ወይስ ኮሎኔል መንግስቱ በዚምባብዌ መጠለያ እንዳገኙ በሱዳን የወደፊት መጠለያ ለማዘጋጀት ታስቦ ይሆን ?

"የኢትዮጵያ ድንበር አልተደፈረም። የሚወራው ወሬ ውሸት ነው" የሚል ማስተባበያ ከኢሕአደግ ባለስልጣናት ሊቀርብ ይችላል። መፍትሄው ግን ቀላል ነው።

በአገራቸው የአንድነት ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያውያን የኢሕአዴግን ጥቂት ባለሥልጣናት ማመን ካቆሙ ብዙ ሰንብቷል። ስለዚህ **በአስቸኳይ ገለልተኛ የሆነ ኮሚሽን ተቋቁሙ ከሱዳን በኩል የተፈጸመውን ጥቃት እንዲሁም "ተፈርሞ ለሱዳን ተሰጠ" ስለተባለው የኢትዮጵያ ግዛት መርምሮ ለሕዝብ ይፋ እንዲያደርግ እጠይቃለሁኝ።** የኢሕአዴግ መሪዎች እውነት ከእነርሱ ዘንድ አለ ብለው የሚያምኑ ከሆነ መርማሪ ኮሚሽኑ ነጻ ያወጣቸዋል።

በአገሩ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመወሰን መብቱ መረጋገጥ አለበት።የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልወሰነው ማንኛው ስምምነት ሆነ ውል ወደፊት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። አይኖረውምም !!!!!

ኦማር አልባሽር ከአማካሪዎቻቸው ጋራ ይሄን ጊዜ "ኢትዮጵያ የሚረባ ሰው የላትም" እያሉ ያፌዙ ይሆናል። ነገር ግን በጋራና በአንድነት ለዚህ ወራሪ ኃይል መልስ የምንሰጥበት፣ ኢትዮጵያ ልጆች እንዳሏት የምናሳውቅበት ጊዜው አሁን ነው። በውጭ አገር፣ በአገር በውስጥ፣ በገጠርና በከተማ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አጼ ዮሐንሶች እንዳሉና አገርን የሚሸጡ ለጊዜው የተመቻቸው እጅግ በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ የምናውጅበት ጊዜው አሁን ነው።

በዚህ አጋጣሚ በአራት ኪሎ የሚገዛውን አምባገነን ስርዓአት እንደ ምሰሶ ሆናችሁ የምትሸከሙ የኢሕአዴግ እንዲሁም የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት አባላት የሆናችሁ ሁሉ፣ ከዝምታ የምትወጡበት ጊዜው አሁን እንደሆነ ላሳስብ እወዳለሁ። እርስ በርስ ከፋፍሎ የተበተባችሁን የነ አቶ በረከት ስሞንና አቦይ ስብሃት ነጋን መረብ በጣጥሳችሁ የጀግናውን የአጼ ዮሐንስን ኮቴ በመከተል ኢትዮጵያን የማዳን ታሪካዊ አደራ አለባችሁ።

እግዚአብሄር አገራችን ኢትዮጵያን ይጠብቃት !